# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *


**የካቲት** 1999 **ዓም**

## *መንፈሰ የካቲት--የዓመፅ የትግል ጥሪ*

***መታደልም መረገምም ከአንዴም በላይ ተጣምረው ሊመጡ የሚችሉ መሆናቸውን እያየን ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዱ የካቲት ተሸኝቶ ሌላው የካቲት ሲመጣ ዘወትር በትግል ላይ መገኘቱ አንድም የታሪክ ሰሪነቱን ፀጋ ሲያበስረን÷ በሌላ በኩል ደግሞ ከየካቲት 66 እስከ ዘንድሮ የካቲት ሁሌም የትግልና የዓመፅ ጥሪ ሲስተጋባ መሰማቱ በጫንቃችን ላይ የሰፈረው የጭቆና ቀንበር ሊወገድ አለመቻሉን፤ ሰቆቃችን የቀጠለ ሊቀጥልም የሚችል መሆኑን ያሳየናል:: ለትግል የተዘጋጀ ሕዝብ መኖሩ ግን ከሁሉም በላይ አኩሪ ክስተት ነውና መንፈሰ የካቲትን በማደስ ለቀጣይ አመርቂ ትግል ለተደራጀ አመፅም ነጋሪት መጎሰሙ ለኢትዮጵያ ህልውናና ለህዝቧ ደህንነት ቸር አብሳሪና ብሩኅ ተስፋም ፈንጣቂ ነው::***

***ከየካቲት 66 እስከዛሬ ህዝባችን የተጓዘበት የታሪክ ጎዳና በህዝብ ትግልና መስዋዕት የታጀበ፤ በአምባገነኖች ዕብሪትና አረመኔነት የተወሳሰበ፤ ድልና ሽንፈትን ያቀፈ፤ ጀግንነትንም ክህደትንም ያሳየ ነበር:: የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ አጥተውና የሕዝብም ትግል ከድል ታግዶ÷ ጨቋኙ ወታደራዊ መንግሥት በገንጣይ ኃይል ተተክቶ÷ የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ አሳሳቢና አልፎም ራሱን የህገሪቱን ህልውናዋን በአስጊ ሁኔታ ውስጥ የከተተ ሆኖ ቆይቷል:: ለየካቲት ፍንዳታ ዋና ምክንያት የነበረው የመሬት ለአራሹ ጥያቄ በደርግ ተወላግዶ፤ አርሶ አደሩ የመንግሥት ጢሰኛና መብት አልባ ሆኖ፤ በኮታው ሥርዓት ምርቱን እየተቀማ የነበረበት አሰቃቂ ሁኔታ ዛሬም ቀጥሏል:: በተለይም በብዙሀኑ ላይ ከፋፋይና ዘረኛ ሥርዓት ተጥሎባቸው የሚያርሱትንም ለም መሬት እየተቀሙ፤ ሀገር አልባ ሊሆኑም አደጋው እያንዣበበባቸው ይኖራሉ:: የስቃይና የፍዳ ኑሮ! የዴሞክራሲ ጥያቄንም በተመለከተ በመስኮብ/ሩስያ ይምል የነበረው ግፈኛ ደርግ ሲወገድ የነፍስ አባቴ አልባኒያ ርዕዮቴ ፈላጭ ቆራጭነት የሚል ጠባብ ብሄረተኛው ህወሓት ተተክቷል:: ሀገሪቷ ትላንትም ተደርጎ እነደነበረው ዛሬም ለባዕድ አገልጋይነትና የበላይነት ተዳርጋ ለአምባገነኖቹ የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ሰለባ ሆናለች:: ብዙሀኑ የኢትዮጵያ ሰርቶ አደር ሕዝብ በጭቆና ቀንበር ስር ፍዳውን እያየ ቀጥሏል:: የድህነቱ መጠን ሊገመት ከማይችልበት ደረጃ ደርሶ የነገውንም ተስፋ በማጠውለግ ይበልጥ እያሽቆለቆለ ነው:: በአንፃሩ ደግሞ ጥቂቶች የጠባቡ-ብሔረተኛ ቡድን አባሎችና ጭፍሮች የሀገሪቷን አንጡራ ሀብትና ሕዝቡንም እየዘረፉ፤ ከአለሙት በላይ ከብረዋል:: ሕዝብን እርስ በርስ እያጋጩና እየከፋፈሉ፤ የሕዝቡን ተቃውሞ በአፈናና በግድያ÷ በደም ማፍሰስ÷ ለማጥፋት እየሞከሩ ይገኛሉ:: በጅምላ ፍጅት ተቃዋሚን አስሰቅጥጠው የሽብር ሥርዓትን እያሰፈኑ ይገኛሉ:: ከሠላሳ ሺ በላይ የፖለቲካ እስረኛ ባለባት ኢትዮጵያ÷ አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለም ብሎ ነጋ ጠባ ሳያፍር የሚቀጥፍ አገዛዝ ተሰይሞባታል::***

***ለአያሌ ዓመቶች የቀይ ሽብሩ ቁስል በሕዝብ የትግል ተሣተፎ ላይ ከባድ ጉዳትን አድርሶ፤ የሀገራችን ዕጣ ለጥቂቶች የሞት ሽረት ጉዳይ÷ ለሌላው ደግሞ እንደ ኮረንቲ ሽቦ የማይነካ ሆኖ ቆይቶ ነበር:: ያን መንፈሰ የካቲት ድሮም ያቀጣጠሉት የተወሰኑት ቀደም ብሎ ሁኔታዎችን በመረዳት የተገነዘቡትንም ለብዙሃኑ በማስረዳት ፀንተው ትግሉን በመቀጠላቸው፤ ህወኃት-ኢህአዴግ የሥልጣን ባለቤት ከሆነበት አንስቶ በትንንሽ ጥቅም የሚሸነገሉት ክፍሎች ጩኸት የኢትዮጵያን የድረሱልኝ ጉልኅ ጥሪ ሊያፍን***

ቢነሳም ወጣትና ሽማግሌው፥ ተማሪውና አስተማሪው፥ አርሶ አደሩና ከተሜው ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅዖ ለትግሉ በማድረጉ ለረጅም ጊዜ የተከፈለው መስዋዕት በግንቦት 97 ለተከሰተው የላቀ ንቃተ ህሊናና የአመፅ መንፈስ አብቅቷል። የየካቲት 66 አብዮት ለረጅም ጊዜ በተካሄደው የተማሪዎችና የላባደር ትግል፣ የአርሶ አደሮች አመፅና የሌሎችም እምቢተኛነት ውጤት እንደመሆኑ መጠን በ97 ዓም የተከሰተው ታሪካዊ፥ ሕዝባዊ ትግልም እንዲሁ የብዙሀኑ የዓመታት ትግል ውጤት ነበረ። ይህ ደግሞ የታሪክ ዕይታቸው ሚዛናዊ ለሆነው ሁሉ በግልፅ ሊታይ የሚገባ መሆን ያለበተ ጉዳይ ነው። ባልለማ ባልታረሠ ባልለሠለሠ ማሳ ላይ ጤፍ ተዘርቶ ጥሩ ምርት እንደማይጠበቅ ሁሉ በጥቂት ወራት የፖለቲካ ሥራም ሀገራችን ውስጥ ተዓምር አልተከሰተም። ዓመታት የፈጀው የፖለቲካ ሥራ ለአመፅ መንፈስ ግንባታ ለመነሣሣት ቢያበቃም በበቂ ስላልተደራጀ ለድል አላበቃም። ይህን ስናይ፥ በሁሉም መስክ ገና ብዙ ሥራ፥ መራራ ትግልና ከባድ መሥዋዕት እንደሚጠብቀንም ግልፅ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ጃንሆይ ምን አጠፉ" እያለ በሚጠይቅበት በቀድሞው ሁኔታ ላይ አይደለም የሚገኘው። "ህወሓት-ኢሐአዴግ ምን ያላወደመው አለ" ብሎ አገዛዙን በጠላትነት ፈርጆ ሊያስወግደው መፈለጉን ግልፅ አድርጎ በመታገል ላይ ነው ያለው። ይህ ለትግል መሠረት የሆነ ንቃት ሰፍኖ እያለ፥ ትግሉ ጎልቶ አለመታየቱ ደግሞ በግድ የአደራጆችና የመሪዎችን ድክመት እንድናነሳ ይገፋፋናል።

በየካቲት 66 በህቡዕ ከተደራጀው ኢሕአፓ በስተቀር ሌላ የሚታወቅ የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም። ኋላ ሌሎች ቡድኖችና ድርጅቶች ብቅ ብቅ ቢሉም፥ በአብዛኛው ከአገዛዙ ጋር በመሰለፋቸው በተቃዋሚነት ተሰልፎ ለተወሰኑ ዓመታት የሁሉንም ጥቃት ተቀባይ የነበረው ኢሕአፓ ብቻ ነበር። ኢሕአፓም ለብዙሀኑ የድርጅትን ምንነት አስተምሮ፣ አደራጅቶ ያታገለና ያስተማረ ድርጅት ሲሆን፥ በትግሉ ሂደትም ራሱ ከስህተቱና ከተመክሮው እየተማረ ሊሻሻል በቅቷል፣ ወደፊትም እየታገለ እየተማረ ይቀጥላል። ያ መራራ የትግል ዘመንና የተከፈለው ከባድ መስዋዕት በአጠቃላይ ሕዝቡን ብዙ አስተምሮ ለሚያደራጁ ሁሉ መሠረት ፈጥሮ ዛሬ ድርጅት በየጎራው ተበራክቶ ለማየት በቅተናል። ድርጅቶች ቢበዙም በአሁኑ ወቅት ብዙዎቹ በኢትዮጵያዊነና በሀገር-አቀፍነት ከመደራጀት ይልቅ በብሄረሰብ ደረጃ የተዋቀሩ መሆናቸው ደግሞ በከፊል ሁናቴው ግድ ያለው ሲሆን ባመዛኙ ደግሞ ህወሓት ሆንብሎ ካራገበው የጠባብ ብሔረኛነት ፖለቲካ የመጣ ነው። ይህ የህወሓት የዘር ፖለቲካም ችግሮችን መቀፍቀፉ አልቀረም። የወደቀው የመንግሥቱ አገዛዝ፥ ታጋይ ዜጎችን ጨፍጭፎና በሽብር የሕዝብን ቅስም ሰብሮ በመቆየቱ ይህ ሁኔታ ለጠባቦች በር ከፍቶ ማመቻቸቱ፥ መመቸቱ ደግሞ የሚካድ አይደለም። ለዓላማና ለሀገር የተከፈለ መሥዋዕት በአሉታዊ የተተቸበት፣ የሽብር ሰለባዎች እየተወገዙ ወንጀለኞች የፖለቲካ መድረኩን ያጣበቡበት፣ ራስን ከሀገርና ከወገን ማስቀደሙ በብልህነት የተፈረጀበት ሁኔታ ሰፍኖ ቆይቶ ለህወሓት ማመቻቱም ገሃድ ሃቅ ነው። የፖለቲካ ትግልም ሊሰጠው የሚገባው ሙያተኛ ትኩረት ተነፍጎት ተመክሮም፥ ዕናቱም ያላቸው እያነሱ መሄዳቸው ደግሞ ዛሬም የሚታይ ክስተት ነው። በመሆኑም ተቃዋሚ ኃይሎች አንድም ስለ ጠላት-ወዳጅ ግምገማ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የድርጅትን ሥራና ሚና በተመለከተ ራሱ ግንዛቤያቸው የተሳሳተና የጫጫ በመሆኑ፥ የሕዝብን የአመፅ መንፈስ መርተው ለድል ሊያበቁት አልቻሉም።

በማንኛውም ትግል ጅማሮና ሂደት የመጨረሻ ግብን በቅድሚያ ማወቅ የግድ ነው። እግሬ በወሰደኝ ብሎ ጉዞ በፖለቲካ ትግል ውስጥ የለም። በመሆኑም ትግል ሲጀመር ማንን ለመታገል እንደሆነ፣ ለማንና ለምን ትግል እንደሚካሄድ አስቀድሞ ማወቅ ያሻል። የፖለቲካ ሁኔታም ቀዝቃዛ ሥፍራ ላይ እንዳለ የገረወይና ቅቤ የረጋ ሳይሆን የሚቀልጥና በየጊዜው የሚለዋወጥ በመሆኑ ሁሌም ተጨባጭ ሁኔታውን ከስሜታዊነት ርቆ በጥሞና ማጤን መመርመር የግድ ነው። በዚህም መሠረት፥ በሀገሪቷ ውስጥ የሰፈነውን ዋነኛ ወይም ተቀዳሚ ቅራኔ ማወቅ ይኖርብናል። ይህን በተመለከተ ኢሕአፓ ገና በ1967 ዓ.ም. ያኔ ተሓህት ይባል ከነበረው፥ ዛሬ ህወሓት ከተባለው ጋር የተጋጨው ይህ ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅት፥ የኢትዮጵያ ዋነኛ ቅራኔ በብሄረሰቦች መሀል ያለው ነውና ሊፈታ የሚችለውም እያንዳንዱ ብሄረሰ ተገንጥሎ የራሱን ነፃ ሬፑብሊክ ሲያቋቁም ብቻ ነው ብሎ በመደምደሙ የተነሳ ነው። ዛሬ ታሪክ የተረሳ መስሏቸው ኢሕአፓ በተጨባጭ ለግንጠላ ቆመ የሚሉ በዚያን ወቅት ድርጅቱ የወሰደውን አቋም ይዘት ከመሳታቸውም ሌላ ኢሕአፓ መገንጠል ወይ ሞት ብለው ከተነሱት ከእነ ተሓህት/ህወሓት ጋርም ያደረገውን የሞት ሽረት ትግል ይክዳሉ። ለማንኛውም ቅራኔን በአግባብ መረዳቱና በተገቢው ሚዛን መፈረጁ ወሳኝ ጉዳይ ነው። በ1966 አብዮት ወቅት ደርጉን ወዳጅ ኃይል ብለው የፈረጁና ከጎኑም የተሰለፉት በጥፋቱ ቢያጅቡትም ራሳቸውን ዞሮ አጠፋቸው እንጂ ወዳጅ አልሆናቸውም። ከእነዚህ ዓይነቱ ተመክሮ መማር ይገባናል። አምባገነናዊና አሸባሪውን የመለስን አገዛዝ በወዳጅነት መፈረጅም

ችግር አምጥቷል። ህወሓት/ኢሕአዴግ የችግሩ ጎሬና ምንጭ መሆኑ በተወሡኑ ክፍሎች በበቂ አልተጤነም።

ማንንም ለመውቀስ ሳይሆን ለትምህርታዊነታቸው አንዳንድ ግንዛቤዎችን ልንይዝ ይገባል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነውና÷ ተቃዋሚ ኃይሎች የጋራ ድላቸውን ለማረጋገጥ ዕውን ማድረግ ያለባቸውን ጠንካራ ህብረት መመስረት ባለመቻላቸው÷ የመሠረቱትንም በዚያው ደረጃና ሁኔታ ለማስቀጠል ባለመቻላቸው፤ የመለስ አገዛዝ ተጠቃሚ ሆነ። ይህ ድክመት የሚያመጣውን ጉዳት በተመለከተ ብዙ ተመክሮ የነበረ ቢሆንም÷ ከዚህ ምንም ዕውቀት አልተገበየም። ሁሉን አቀፉ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት ከሁለት ዓመት ጥረት÷ ውይይትና ዝግጅት በኋላ የስንቱን ሻጥርና ደንቃራ ተወጥቶ ቢመሰረትም ሳይውል ሳያድር ሊያፈርሱት የሞከሩ ክፍሎች ነበሩ÷ ገና በአዲስነቱ ተረባርበው ሊከፋፍሉት ቻሉ። ይህ የመጀመሪያ ጥፋት ደግሞ በሌሎች ተከታታይ ጥፋቶች ታጀበ። የምርጫው ህግና ቦርድ ካልተለወጡ በምርጫ አንካፈልም እንዲባል በምስረታው ጉባዔ ወቅት የተደረሰበት ስምምነት ወዲያው ተተወ። በምርጫ ከተገባም በኋላ ቢያንስ የህወሓትን ማንነት በሚያውቁት የተጠበቀው ማጭበርብረም ሊከሰት እነደሚችል ተጠቁሞም ነበር። እንደተፈራውም አስታራቂና ክርክሩን የሚዳኙ ክፍሎች ተብለው የተወሰዱት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚፃረሩ ባዕዳንና የህወሓት የራሱ የምርጫ ቦርድ የተባለው በመሆናቸው ለአገዛዙ የሚያመች ውሳኔ ላይ ተደርሶ የሕዝብ ድምፅ ቅሚያው ህጋዊ ተባለ ።

ይህን በመቃወም ሊደረግ የተጀመረው ትግል÷ በያለንበት ግራ ሲያጋባን ቆይቶ ነበር። በተለይም በብዙ ቅስቀሳ የተዘጋጀው አዲስ አበባን የሙት ከተማ የማድረግ የመጀመሪያው አድማ በተቃዋሚ ኃይሎች መሪዎች በራሳቸው ተሰርዞ÷ ከዚያ በኋላ መድረኩ ለባዕዳንና ለመለስ ዜናዊ መለቀቁ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለና ዛሬ ለምናየው አስከፊ ሁኔታም በር የከፈተ መሆኑ መጠቀስና መታወቅም ያለበት ነው። ያ ሕዝብ ተዘጋጅቶ የጠበቀው አድማ ተካሂዶ ቢሆን ኖሮ በሀገራችን የፖለቲካ ሂደትና ይዘት ላይ ሊያስከትል ይችል የነበረው ለውጥ ሲገመት÷ በዚህ መስክ የባዕዳኑን ምክር ሰምተውና እነሱን አምነው አድማው እንዳይካሄድ ጥሪ ያደረጉት ፖለቲከኞች ትልቅ ሥሕተት መሥራታቸው ዛሬ አሌ ሊባል የማይቻል ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቃተ ህሊና ዛሬ እደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ የረጅም ጊዜ ጥረትን የጠየቀ መሆኑን ስንገነዘብ÷ ዛሬ ያለንበት ሁኔታ የተሻለና ለትግል አመቺ ሆኖ እናገኘዋለን። ምንም እንኳን ከ1997 ዓም የግንቦቱ ምርጫ በፊት በተደረገው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ቋሚና ዘላቂ ድል ባይገኝም፤ በኋላ ለተከሰተው ሕዝባዊ አመፅ ለማዘጋጀት የጠቀመ መሆኑ ሊታበል አይችልም። ሕዝቡ በሂደቱ ውስጥ በቀጥታና በሙሉ ስሜት መሣተፉ ጉድለቶችንም ማየቱና መታዘቡም ትምሕርታዊነት አለው። ከምርጫው በፊትና በምርጫው ወቅት በተካሄዱት የፖለቲካ ቅስቀሳዎች እንቅስቃሴዎች ፍጥጫዎችም አጋዥነትም ጭምር ነበር ሕዝብ ለዓመፅ ዝግጁ ሆኖ የነበረው። ሆኖም ጠንካራ ድርጅትና ብቁ አመራር በማጣቱ፤ የትግል ስልቱም በውል ባለመዘጋጀቱ የነበረው መነሣሣት በአጭር ተቀጭቷል። ከትግል ተመክሮ አንፃር ግን ሕዝብ ጠቃሚ ትምህርት ገብይቷል።

በምርጫው ወቅት የተገለጠውን የሕዝቡን ድምፅ በመቀማትና በመቀልበስ የመለስ ዜናዊ ፀረ ሕዝብ ቡድን በምንም በሰላም ሥልጣንን እንደማይለቅ አሳይቷል። የ97ቱ ግንቦት ምርጫና በህወሓት ላይ ያስከተለው ሽንፈት በሁሉም ዜጋ የተስተዋለ ሃቅ ሲሆን÷ የመለስ ቡድንም ይህን የሕዝብ ድል ለመቀማት የፈፀመው አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ይህን አገዛዝ ለመጣል መንገዶቹ ሁለገብ መሆን እንዳለባቸው ጠቁሟል። የሕዝባዊ አመፅ አካል የሆነው የአድማ እንቅስቃሴ ማለትም ዋና ዋና የሕዝብ ማዕከሎችን የሙት ከተማዎች ከማድረግ እስከ የህወሓት የንግድ ተቋሞችና ቅጥረኞች ላይ ማዕቀብ እስከማድረግ ድረስ ያለው የሕዝብን የአመፅ ኃይል በሚያጎለብት መንገዱ በተደራጀ እንቅስቃሴም መታጀብ እንዳለበት ግልፅ ሆኗል። የኢትዮጵያን ሕዝብ የብዙ ዓመታት ጦርነቶች በርግጥም ጎድተውታል። ጦርነት ሰለቸው ቢባልም÷ ሃሰት አይሆንም። ከዚህ በላይ ግን የሰለቸው÷ የመረረውና እጅ እጅ ያለው በጭቆና መማቀቁ ነው። ሀገሩ ስትዋረድ÷ መብቶቹ ሲረገጡ ማየቱ ነው። ከሁሉም በላይ የጎመዘዘው ሀገሩን ለገንጣይ ኃይል አስረክቦ ስትፈራርስ መመልከቱና በዚሁ አሸባሪነት መጠቃቱ ነው። ስለዚህም የነገው ትግል አቅጣጫና ትኩረት የህወሓትን አደናጋሪና ከፋፋይ ግድብ ያፈረሰና ብዙሀኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተባባረ ሁለገብ ፀረ ህወሃት/አሕአዴግ ትግል ነው መሆን ያለበት።

ከየካቲት እስከ የካቲት ለ33 የትግል ዓመታት ግልፅ ሆኖ የቆየው ሀቅ ደግሞ የሕዝብ ትግል የድል ባለቤት ይሆን ዘንድ የሕዝብ መደራጀት ትብብርና በጋራ ለመታገል የመቁረጥና የመነሳሳት ሁኔታ ሲከሰት ነው። በተናጠል በሚደረግ ትግል ራስን ነጥሎ ማስጠቃት እንጂ ድልን ማስገኘት አይቻልም። የህወሓት/አህአዴግን ፀረ ሕዝብ መንግሥት ገና በእንጭጭነቱ የተባበረ ትግል ቢያጋጥመው እንዲህ ተንዘራፍጦ አይከርምብንም ነበር። በ97ቱ ድኅረ ምርጫ ሁኔታም ክፍፍል ተወግዶ ተቃዋሚ ኃይሎች በኅብረት ቢታገሉ ኖሮ፤ ውጤቱ ከዛሬው በጣም የተለየና የተሻለም ሊሆን ይችል እንደነበር መገመት አያዳግትም። ወጣቱና ሽማግሌው፥ አርሶ አደሩና ሠራተኛው፥ ከተሜውና ገጠሬው እንዲሁም የሕዝቡ ግማሽ አካል የሆኑቱ ሴቶች፥ ሁሉም ሆ ብለው ተነስተው በነበረበትና ሰላማዊ በነበረውም ትግል አርዕድ አንቀጥቅጥ ኃይላቸውን አሳይተዋል። ነገር ግን ከገዢው ቡድን አምባገነናዊነትና አሸባሪነት ባህሪ የተነሣ ሠላማዊ የነበረው ሂደት እስራትን፥ ድብደባን፥ ሰቆቃን፥ የብዙ ዜጎችን የደም መፍሰስን ወዳስከተለው ሂደት ተሸጋገረ። ሕዝቡም ያስገኘው ድል ሊነጠቅ ቻለ። በወቅቱ ተነሳስቶ የነበረውን ሕዝብ ተቃዋሚ ኃይሎች በመከፋፈላቸውና በበቂም ባለማደራጀታቸው መርተው ለድል ለማብቃት አልቻሉም። ይህ የክፍፍል ሁኔታም ለሕዝብ የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰው ከዋናው ጠላት ጋር መሠለፍ ለሚፈልጉት ፖለቲከኞች አመቺ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል። የዚህም ትምህርቱ የድል ጎዳና በተባበረ ትግል ላይ መመስረት እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ድርጅቶች በሰማዕት ደም የተገኘውን ተመክሮ አክብረው፤ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ የሚለውን ወይም የድርጅት ውሱን ጥቅም ከሀገር በላይ የሚያስቀምጠውን ማንኛውንም አቋም አስወግደው፤ ሀገር አድን በሆነ የጋራ ፕሮግራም ወይም ግብ ዙሪያ ተሳብስበው፤ ተቀናጅተውና አብረው መታገል መቻል አለባቸው። ከሀገር በፊትና በላይ ማንም የለምና በርዕዮት ወይም በሥልጣን ጉጉት ዙሪያ ለመጋጨቱና ለመለያየቱ ጋባዥ ሁኔታውም ሆነ ጊዜው ከቶ ሊኖር አይገባምና ነው።

ለሀገራዊ ትግሉና ለመላው ሕዝብ ዘላቂ ጥቅምና ለድሉም ቅድሚያን መስጠት ደግሞ በመሠረቱ በሕዝብ የበላይነትና ወሳኝነት ላይ እምነት መኖሩን የሚያመለክት ነው። ለትግልም ሆነ ለሚመሰረተው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋናው ጉዳይ በሕዝብ ወሳኝነት ላይ ዕምነት መኖሩ ነው። ድርጅቶች የየራሳቸውን ፕሮግራም ወይም ዕምነት በሕዝብ ላይ ለመጫን ከመዋደቃቸው በፊት፥ ዛሬ ያለው አቢይ ተግባር ሀገርን ማዳኑ በመሆኑ ለዚሁ ዓላማ በጋራ ተሰልፈው የሀገርን ህልውና ሊያረጋግጡና ጨቋኙን አገዛዝም ሊያስወግዱ ይገባቸዋል። የሥልጣን ድልድሉን በተመለከተ ምርጫውን ለሕዝብ መተው ይኖርባቸዋል። ግማሽ ዴሞክራሲ ማለትም ዴሞክራሲ ለተወሰነ ክፍል ጭቆና ለሌላው ለሚል መርህ ልንታገልለት ቀርቶ ልናስበው የምንፈልገው ጉዳይ መሆን የለበትም። የህወሓት/ኢህአዴግ ዴሞክራሲ ለብዙሀኑ ከዴሞክራሲ የተጣላ ጭፍን አምባገነንነት ነው። በዚህም ረገድ የምንታገልላት ኢትዮጵያም የጥቂቶች ብቻ ሳትሆን የሁሉም የምትሆንና ዴሞክራሲያዊ መሠረት የሚኖራት መሆን ይገባታል። ያለፉትን የጭቆና ሥርዓቶችም ሆነ የህወሃትን ጠባብ ብሄርተኛነት የሚያስወግድ እንጂ የሚያድስ ሁኔታ ሊታሰብ አይችልም። ይህን በመረዳትም ለብሄረሰብ መብት እንታገላለን የሚሉትም በበኩላቸው ለሀገርም ለሕዝብም ጠቃሚነት እንደሌለው የተረጋገጠውን የመገንጠል አማራጭ ትተው ለአንዲት በዕኩልነት ላይ የቆመች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመታገል መነሳትና አሁን ያለውን አስከፊ ሁኔታ በጋራ ለመለወጥ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ይጠበቅባቸዋል። በየካቲት 66ና ከዚያም በፊት በሀገራችን ለውጥ ፈላጊዎች በብሄረሰብ በሃይማኖት ሳይከፋፈሉ በመታገላቸው ውጤት አስገኝተዋል። ህብረ ብሄር የሆነውም ኢሕአፓ በሀገራችን የትግል ታሪክ አኩሪ ምዕራፎችን የፃፈው፥ ለኢትዮጵያ የሚታገሉ ታጋዮችን ከየብሄረሰቡ አሰባስቦ በማቀፉ መሆኑም የሚዘነጋ አይደለም። ይኸው ያለፈው ተመክሮ፥ ድርጅቶች በምንም ሁኔታ ሕዝብን ሊተኩ እንደማይችሉና ከሕዝብ በላይ ነን ብለው በሁሉን አዋቂነትና ወሳኝነት ከተሰየሙ ጉዳት እንደሚከተል በሚገባ አሳይቷል።

የትግላችን ግብ ሀገሪቷን ከመለስ አገዛዝ አላቅቆ፤ ካንዣበበባት አደጋ አድኖ ህልውናዋን ማስከበር መሆኑ ግልፅ ነው። ይህ ሁሉን ቀዳሚ ግብ ደግሞ የተለየች ኢትዮጵያን ለመመስረት፥ ማቀድን ማለምን የግድ ይላል። የተለየች ስንልም በመሠረቱ ዴሞክራሲን፥ ዕኩልነትን ዕውን ማድረግን ይመለከታል። ኢሕአፓ ለሰፊው ህበረተሰብ የሚበጅ ሠፊ ዴሞክራሲን የትግሉ መመሪያ አድርጓል። ጭቁኑንና ሰርቶ አደሩን ሕዝብ ከሌሎቹ ዕኩል ባለሀገር ማድረግና ፍትኅ ርትዕን፥ የህግ የበላይነትን ማስፈን ዋና ተልዕኮው ነው። ሰርቶ አደሩን ለብዝበዛ አለማጋለጥ፤ የሥራና የኑሮ ዋስትናውን ማስከበር፤ የላቡና የምርቱ ተጠቃሚ ማድረግ፤ የህብረተሰቡን የትምህርትና የጤና አገለግሎቶች ማስፋፋትና

ለሁሉም ማዳረስ፤ የሴቶችን መብት የሚፃረሩትን ሁኔታዎችና ልምዶች ማስወገድ፤ በሕዝብ መሀል ሰላምና ዕኩልነትን ማስፈን፤ ሀገርን በኤኮኖሚ መገንባት፤ ነፃ ምርጫን በሥራ ማዋል÷ማክበር...ወዘተ መጪዋን ኢትዮጵያ የሚገልጿት እንዲሆኑ ኢሕአፓ ይመኛል ይታገላልም፡፡ ነገር ግን በቅድሚያ ሀገርን ለማዳን መታገል እንዳለበትም ጠንቅቆ ያውቃል፡፡

ያለፈውን ስህተት ላለመድገም የትግላችንን ዒላማዎችና ዓላማዎች ጥርት ባለ መንገድ መገንዘብ ማወቅ አለብን፡፡ ካለፈው በመማር ደግሞ÷ ሞቅ ሞቅ ጠንካራ ድርጅታዊ ሥራን፤ ግርግር መደራጀትን ሊተኩ እንደማይችሉ ማወቅ ይገባናል፡፡ ሕዝብን ሆ ብሎ እንዲነሳ ማድረጉን በተመለከተ ለዓመታት በተከፈለው መስዋዕትና በተካሄደው ትግል የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ሕዝብ ነቅቶ ለትግል መነሳቱ የሚታይ ቢሆንም÷ መደራጀትን በተመለከተ ግን ገና ብዙ ሥራ እየጠበቀን እንዳለ መካድ የለበትም፡፡ ስብስቦች በሚገባ የተዋቀሩና የተደራጁ ሆነው አልተገኙም፡፡ ድርጅቶች በአጠቃላይም በመጠናከርና በስፋት በመዋቀር ደረጃ ገና ብዙ ይቀራቸዋል ቢባል ስህተት አይደለም፡፡ በህቡዕ የሚንቀሳቀሱት ደግሞ ህቡዓዊነት የሚያመጣውን ችግር ሁሉ መሸከም ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ የአገዛዙ የአፈና መዋቅር ደግሞ እንቅልፍ አልባ ሥራውን የሚሰራ በመሆኑ÷ ድርጅቶችን በማዳከም ዘመቻው እስካሁን ለቀቅተኛ ሆኖ አልታየም፡፡ ይህ ሁሉ ሀቅ ቢሆንም÷ ድርጅታዊ ሥራ በተፈለገው ፍጥነት የምንመኘውን እመርታ ባያገኝም፤ በየካቲት 66 የተከሰተውን የመደራጀት መንፈስ÷ ችሎታና ደረጃ ባያሳይም፤ ቀሰ በቀስ እያደገና እየተሻሻለ መምጣቱ የሚታይ ነው፡፡

የህብረተሰቡ ብዙሃን የሆኑትን ወጣቶችና ሴቶች በመንፈስ የካቲት የሚያነሳሳ የትግል እንቅስቃሴና ቅስቀሳ አስፈላጊ ነው፡፡ ትውልድ በደፈናውና በጅምላው ትግል ይጠላል ብሎ መደምደም ስህተት ከመሆኑ በላይ በግንቦት 97 ደግሞ የአሁኑ ትውልድ ድፍረቱን-ቆራጥነቱን አስመስክሯል፡፡ ብዙሃኑ በሀገራቸው ጉዳይ ያገባናል ብለው ለትግል ጆሮአቸውን እንዳይሰጡ ሥርዓቱ ወጣቱን በአጓጉል ልምዶች በመጥመድ፤ የአደንዛዥ ዕፆችና የስካር ልምድን በማስፋፋት፤ ዝሙትንና የኤይድስ በሽታን ስርጭት የሚያራገብ ሁኔታዎችን በማስፈን፤ የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው፡፡ ሀገራዊ ስሜትና የትግል ስሜት ያላቸውን ወደ ስደት በመገፋፋት፤ የትግል ፀር የሆኑ ዕምነቶችን በመደገፍና በሃይማኖትና በብሄረሰብ በመከፋፈል...ወዘተ የመለስ አገዛዝ የወጣቱን ሀገራዊ ፍቅርና የትግል ስሜት ለማግደል ቀን ተሌት እያጣረ ነው፡፡ ስለዚህም ሀገር አድን ትግላችን በቅድሚያ ወጣቱን ከህወሓት ወጥመድ ማራቅ÷ ማውጣትን ይጠይቃል፡፡ ታጋይ መሆን የሚገባው ኃይል ባክኖ ወይም ለስደት ተዳርጎ እንዳይገኝ÷ እንዳይቀር አስፈላጊው ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህ ወሳኝ ትግል ደግሞ ድርጅቶች በቅድሚያ ራሳቸውን በመንፈስ የካቲት አንፀው በቃል ሳይሆን÷ በገቢር ለወጣቱ ሁሉ አርዓያ እንዲሆኑ ይጠራቸዋል፡፡ ተያይዞ ገደል ዓይነት ሁኔታ እንዳይፈጠር የመሪና ተመሪ ሚናና ችሎታም ተገቢ ቦታውን ይዞ መገኘት አለበት ማለት ነው፡፡ ድርጅቶች ራሳቸው የአንድነት እንጂ የክፍፍል፤ የኢትዮጵያዊነት እንጂ የጥበት ወይም ትምክህት ነፀብራቅ ሊሆኑ ከቶም አይገባም ማለት ነው፡፡

በሀገራችን ዛሬም እየተጎሰመ ያለው ነጋሪት የትግል÷ የአመፅ ጥሪን የሚያስተጋባ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የተከፈለው መስዋዕት ሁሉ÷ ከንቱ ሳይሆን ዛሬ ለደረስንበት ንቃትና የትግል ደረጃ መሠረት ነው፡፡ ትግልንና ድልን በሥልጣን መያዝ አለመያዝ ብቻ ወስነው የሚተምኑ ይህን የተጠቀሰውን ሀቅ ይስቱታል፡፡ የፈሰሰው ክቡር ደም እያሰማ ያለው ነጎድጓዳዊ ድምፅ ከጆሮአቸው አይገባም፡፡ በሥልጣን ያለው የመለስ ቡድን ግን የታሪክ ሂደትና አቅጣጫ ወደ መቃብሩ እየወሰደው መሆኑን የተረዳ መሆኑ ባያጠራጥርም÷ ከሥልጣኑ ለመቆየት ገና ብዙ ደም ለማፍሰስ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ሀገርን ለባሰ ጥፋት ለመዳረግ በመቅበጥበጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ሀገሪቷ÷ ከፊቷ የስርየትም÷ የጥፋትም ጎዳናዎች ተደቅነውባታል፡፡ በየትኛው መጓዝ እንደምትገደድ የሚወስነው ግን÷ የመለስ ቡድን ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ሕዝቡ መሆንም አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ወሳኝ ቦታ ተገኝቶ ሚናውን ለመወጣት ደግሞ በጋራ ተደራጅቶ መነሳት ይገባዋል ማለት ነው፡፡ መደራጀት፡፡ ማመፅ፡፡ በተዋጣለት ስልት በጋራ መታገል፡፡

የካቲት በየካቲት ሲተካ መልዕክቱ ያው ነው--ሀገሩን ለማዳን ሕዝብ አብሮ መነሳትና በጋራ በቆራጥነት በፅናት መታገል አለበት የሚል ነው፡፡

በተባባረው ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ያችንፋል!!!